# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 35 ኛ ሳምንት

## የጌታ ጸሎት

**ዓላማ**

- ✥ የጌታን ጸሎት መማር

**ምንባብ**

- ✥ ሉቃ 11

**መግቢያ**

- ✥ በአማርኛ *"አባታችን ሆይ"* ብለን የምንጸልየውን የጌታ ጸሎት ታውቃላችሁ? ይህ ጸሎት ማን እንደሠጠንስ አውቃችኂል?
- ✥ ዛሬ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸውን ጸሎት *"አባታችን ሆይ"* ን እንማራለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

(1) ቅዱስ ጴጥሮስን ሄሮድስ ለምን አሠረው ?

(2) ከእስር እንዲወጣ ጴጥሮስ ማን ረዳው ?

(3) ቅዱስ ጴጥሮስ በእስር በነበረ ግዜ ወዳጆቹ ምን ያደርጉ ነበር?

**ትምህርቱ**

- ✥ አንድ ቀን ሐዋርያት ጸሎት እንዲስተምራቸው ጌታችንን ጠየቁት፡፡
- ✥ እርሱም ስትጸልዩ እንዲህ በሉ አላቸው ፡-

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ -----------------------------------------------
መንግስትህ ትምጣ፣ -----------------------------------------------------
ፈቃድህ በሰማያት እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፣-----------------------------
የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ፣---------------------------------------------------
በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደለሉን ይቅር እንደምንል፣----------------------------
አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን፣--------------------------------------------------------
ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፣----------------------------------------------------------
መንግስት ያንተ ናትና -----------------------------------------------------------
ኃይል ክብር ምስጋና ለዘለአለሙ አሜን፡፡------------------------------------------

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ፣
ትምጻእ መንግስትከ
ወይኩን ፈቃድከ፣በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር፣
ሲሣየነ ዘለለእለትነ ኃበነ ዮም፣
ኅድግ ለነ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንኅነኒ ንኅድግ
ለዘ አበሰለነ
ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት፣
አላ አድኅነነ መባልሐነ እምኩሉ እኩይ
እስመ ዚአከ ይዕቲ መንግስት
ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

- ✥ *"አባታችን ሆይ"* ብለን የምንጸልየው ጸሎት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ነውና ***"የጌታ ጸሎት***" ተብሎም ይጠራል ፡፡
- ✥ በዚህ ጸሎት ጌታችን የሚከተሉት አስተምሮናል፡፡

1. እግዚአብሔር ማመስገን
2. የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸም መጋበዝ
3. የእለት ምግባችንን መጠየቅ
4. ይቅር እንዲለን ሌሎችን ይቅር ማለትና ንስሐ መግባት
5. ከፈተና እንዲያወጣን መለመንና
6. ከክፉ እንዲጠብቀን መጸለይ፡፡

- ✥ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን እርሱም አባታችን ነው፡፡ ለዚህም ነው አባታችን ሆይ ብለን እንድንጠራው ያስተማረን፡፡
- ✥ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች መኖርና እግዚአብሔር የልጅነትን ባሕርይ ትዕዛዙን በመጠበቅና ሌሎችን በመውደድ ማሣየት አለብን፡፡

**መዝሙር**

አማን በአማን (4)

መንግስተ ሥላሴ ዘበኣማን (4)

**ጥያቄዎች**

(1) ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ------------ የተባለውን ጸሎት አስተማራቸው፡፡

(2) በዚህ ጸሎት እግዚአብሔርን ምን እንለዋለን?

(3) ከዚህ ጸሎት እግዚአብሔርን ምን እንለዋለን?

(4) ከእኛ ምን ይጠበቃል? በተማራችሁት መሠረት ለመምህርና ቤተሰብ አስረዱ፡፡

**ይቆየን፡፡**